# የዘመኑ የእምነት እንቅስቃሴ

## መሠረቶችና መዘዞች

ግርማዊ

አሳታሚ - ቤሪያ የሕትመት ኩባንያ
1990 ዓ.ም.

# ማውጫ


ምዕራፍና ርእሰ-ጉዳይ — ገጽ

መግቢያ - ውድ ተደራሲያን — 10

1. የነ ሐገን "ሬማ" ስንክሳራዊ ገጽታዎች — 14

2. ኢየሱስ በሲኦል ዳግም ተወልዷል? — 23
   - ሰው በኃጢአት በወደቀ ጊዜ ከመለኮትነት ወደ አጋንንትነት እንደ ተቀየረ
   - መንፈሳዊ ሞትና የኢየሱስ ዳግም መወለድ
   - ክርስቶስ ለሰይጣን ተሠውቷል?
   - የወንጌው ስብከት
   - የኢየሱስ ሁለት ሞቶች

3. እምነት በእምነት ላይ — 42
   - የእምነት ቀመር
   - በኢየሱስ ስም የጠየቅነውን ሁሉ እናገኛለን

4. ፈውስና ተአምራት — 49
   - ለአማኝ መታመም ተገቢ አይደለም
   - አሉታዊ ቃል በሽታን ያስከትላል
   - የበሽታ ምልክቶችን መካድ
   - የሕክምና ሳይንስ
   - አማኞች ከቶውንም ታመው መሞት የለባቸውም
   - አማኞች ከ70 ዓመታት በፊት መሞት የለባቸውም
   - ኢዮብ
   - ፈውስና ተአምራት በመጽሐፍ ቅዱስ

5. ብልጽግና — 69
   - በምድር ላይ ባለሥልጣኑ እግዚአብሔር ሳይሆን ሰው ነው
   - ኢየሱስና ደቀመዛሙርቱ ባለጠጎች ነበሩ
   - የብልጽግና ወንጌል ኑፋቄያዊ ባሕርይ
   - የብልጽግና ችግሮች
   - መጽሐፍ ቅዱስና ድህነት

6. የእምነት እንቅስቃሴ የሐገን ወይስ የኬንዮን? — 85

7. የእምነት እንቅስቃሴ ኑፋቄያዊ መሠረቶች — 89
   - የእምነት ሥነ-መለኮት አዲስ መገለጥ ወይስ ኑፋቄ?
   - የኬንዮን ወንጌል
   - ኬንዮንና ፔንተኮስታል

እንቅስቃሴ

- ♣ ኬንየንና ሜታፊዚካል ኑፋቄዎች

8. ኬነት ሐገንና የእምነት እንቅስቃሴ 94
   - ♣ ሐገን እንደ አስተማሪና ነቢይ
   - ♣ መለኮታዊ ጉብኝት
   - ♣ መለኮታዊ ፍርዶች
   - ♣ የሐገን ሥነ-መለኮት ከሰዎች እንደ ተቀዳ
   - ♣ የሐገን ነቢይነት ሲገመገም

9. የመገለጥ እውቀት 103
   - ♣ ሁለትዮሽ
   - ♣ ስሜታዊውን እውነታ መካድ
   - ♣ ፍጹም እውቀት

10. የእምነት እንቅስቃሴ ከኒው ኤጅ ጋር ሲነጻጸር 108
   - ♣ እውን ክርስቲያኖች ሥጋ-ለባሽ አማልክት ናቸው?
   - ♣ መጽሐፍ ቅዱስ "አማልክት ናችሁ" ሲል...
   - ♣ የመለኮት ባህርይ ተካፋይነት

11. የእምነት እንቅስቃሴና የሳቅ ሪቫይቫል 115
   - ♣ የሳቅ ሪቫይቫል ምንጭ
   - ♣ የቶሮንቶ ብለስንግ ስብሰባዎች ምን ይመስላሉ?
   - ♣ የሳቅ ሪቫይቫል አወዛጋቢ ገጽታዎች

12. የማጠቃለያ መልእክቶች 122
   - ♣ ለእምነት እንቅስቃሴ አራማጆች - ከጂም በከር ተማሩ!
   - ♣ ለክርስቲያን ሕዝብና ለቤተ ክርስቲያን

ማጣቀሻዎች 136

## 3

# *እምነት በእምነት ላይ* (Faith in Faith)

ሴፕተምበር 19፣ 1986 ፍሬድ ፕራይስ የስብከት መልእክታቸውን እያቀረቡ ነበር። እኝህ ሰው በስብከታቸው መሀል፣ "ልክ ነኝ አይደል? ታምናላችሁ?" የሚሉትን ዓይነት የማረጋገጫ ጥያቄዎች የማቅረብ ልማድ ነበራቸው። ብዙዎቹ የእምነቱ ተከታዮች ከሙሉ ልባቸው በሚያቀርቡት የመልእክት አሳብ ላይ የሚስማሙ ቢሆንም፣ ቅጽበታዊ ፈውስን አስመልክቶ በሚናገሩበት ወቅት በአድማጮቻቸው መካከል ውጥረት ይስተዋል ጀመር።

ስለሆነም፣ ፕራይስ በስብከታቸው ወቅት፣ "የሚያድናችሁ እምነታችሁ እንጂ እግዚአብሔር አይደለም! ይህን ታምናላችሁ?" ባሉ ጊዜ፣ አንድ ትምህርቱ ያበሳጫቸው የሰሚናሪ ፕሮፌሰር ዝም ለማለት ባለመቻላቸው ድምፃቸውን አጉልተው፣ "አላምንም!!" ሲሉ እንደ መለሱ ተደምጧል።

ኬኔት ሐገንም "በራስህ እምነት ማመን"("Having Faith in Your Faith") በተሰኘው መጽሐፋቸው ውስጥ ቀጥሎ የተመለከተውን አሳብ አስፍረዋል።

*"በራስህ እምነት ስለማመን አስበህ ታውቃለህ? እግዚአብሔር በራሱ እምነት ላይ እምነት ነበረው! የእምነትን ቃላት ተናገሮ ተፈጽመዋልና . . . በሌላ አገላለጽ፣ በራስህ ቃላት ማመን በራስህ እምነት ላይ እምነት መጣል ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ ነገሮችን ለማግኘት መማር ያለብህ, ይህንኑ ነው – በእምነትህ ላይ እምነት ይኑርህ።"*

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ለዚህ አሳብ እንዲህ ሲል ተቃውሞውን ገልጧል።

*"‹በእምነቱ ላይ እምነት ያለው› የትኛውም አምላክ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና አምላክ ሊሆን አይችልም። አምላክ ነው ለማለትም አይቻልም። ይህ የሜታፊዚካል ኑፋቄዎች ሰብእና–አልባ (impersonal) ኃይል ነው። ምንም እንኳ እነዚህ ሕግጋት፥ ቀመሮችና መንፈሳዊ ሕግጋት በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ ‹እምነት› ቢሰኙም፥ የአዲሱ እምነት ሜታፊዚክስ እጅ–አዙር ቅኝቶች እንደሆኑ ግልጽ ነው።"*



## *የእምነት ቀመር* (Faith in Formula)

ብዙዎች በእምነት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኘውን የእምነት ጽንሰ–አሳብ እንደ "ፎርሙላ" ይገልጻሉ። ይህም የሆነው በእምነት ሥነ–ጽሑፎች ውስጥ "ፎርሙላ፣ ሕግ፣ ደረጃዎችና መመሪያዎች" የሚሉ ቃላት አዘውትረው ስለሚታዩ ነው። ለምሳሌ፣ ሐገን ኢየሱስ በራእይ ተገልጾላቸው፣ "ማንም ሰው፣ በየትም ስፍራ እነዚህን አራት ደረጃዎች ከተወጣ ወይም እነዚህን አራት መመሪያዎች በተግባር ላይ ካዋለ፣ ከእኔ ወይም ከእግዚአብሔር አብ የሚፈልገውን ሁሉ ያገኛል" እንዳላቸው ገልጸዋል። ሐገን ኢየሱስ ሰጠኝ የሚሏቸው "ደረጃዎች" "1. ተናገር፥ 2. አድርግ፣ 3. ተቀበል፣ 4. አውጅ" የሚሉ ናቸው። (በእንግሊዝኛው 1. Say it, 2. Do it, 3. Receive it [claim it], and Tell it.)[1]

ሐገን እንደሚሉት፣ አንድ ሰው እግዚአብሔር አጽናፈ–ዓለሙን ለማንቀሳቀስ ያዋቀራቸውን "መንፈሳዊ ሕግጋት" ካገኘ በኋላ፣ በሕግጋቱ አማካኝነት የሚፈልገውን ሊያገኝ ይችላል።

*"በመንፈሳዊው ዓለም እግዚአብሔር የተወሰኑ ሕግጋትን አዘጋጅቷል። እነዚያ በተፈጥሯዊ ዓለም ውስጥ የሚገኙ ሕግጋት ይሠራሉ! አይደል? ከነዚያ ተፈጥሯዊ ሕግጋት ጋር በምትገናኝበት ጊዜ ይሠሩልሃል። በመንፈሳዊ ዓለምም እንዲሁ ነው። የእምነት ሕግ መንፈሳዊ ሕግ እንደሆነ፣ እግዚአብሔርም ይህንን ሕግ እንዳዘጋጀና ከዚህ ሕግ ጋር በምትገናኝበት ጊዜ እንደሚሠራልህ በማመን ደምድሚአለሁ።"*[2]

ስለሆነም፣ ማንም ሰው ክርስቲያንም ሆነ ኢ–ክርስቲያን ይህንኑ አጽናፍ-አቀፋዊ የእምነት ሕግ በመያዝ "ውጤት" ሊያስመዘግብ ይችላል። ሐገን ስለዚሁ ጉዳይ እንደሚከተለው ያብራራሉ።

*"ነገሩ ያሳሰበኝ ነበር። ማለትም ያልዳኑት ሰዎች ለስኬት መብቃት። በኋላም ተገለጸልኝ – ለካስ እነዚህ ሰዎች ከእግዚአብሔር ሕግ–ከእምነት ሕግ ጋር እየተባበሩ ነበሩ።"*[3]

ፍሬድ ፕራይስ እንደሚሉት፣ ሮሜ 10፡10 የስኬት ፎርሙላ ስለሆነ ማንም ሰው "የሚፈልገውን ነገር ሁሉ – ፈውስ፥ ማንኛውንም ፍላጎት፣ አዲስ ቤት፣ መኪና፣ ወዘተ."[4] በፎርሙላው ውስጥ ሊያስቀምጥ ይችላል።

የእምነት ሥነ–መለኮት ስለ መንፈሳዊ ሕግጋትና ፎርሙላዎች የሚያቀርበው ትንታኔ ከሜታፊዝካል ኑፋቄዎች ዶክትሪን እንጻር የሚታይ መሆኑን ብዙዎች ይናገራሉ። ሜታፊዝካል ኑፋቄዎች የሚያምኑበት አምላክ አጽናፈ–ዓለምን በሉአላዊነቱ የሚያስተዳድር አካላዊ ህልውና ያለው (personal) ሳይሆን፣ ይልቁንም አካላዊ ህልውና የሌለው ኃይል (impersonal force) ነው።

ኬንየን፥ "የማይታዩትን የሕይወት ኃይላት ስለሚያስተዳድሩት ታላላቅ መንፈሳዊ ሕግጋት" ሲናገሩ፥ የሚታፊዝክሱን የዴይዝም አስተሳሰብ ማራገባቸው እንደሆነ ግልጽ ነው – አጽናፈ–ዓለሙ በእግዚአብሔር ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕግጋት እንደሚተዳደር። ይህንኑ የዴይዝም አስተሳሰብ የሚከተሉ ፈላስፎች እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ዓለምን ከፈጠረ በኋላ፣ ራቅ ብሎ

የሚፈቱ የፍቅር መግለጫዎች እንጂ ከቶውንም ‹የፈዋሽነት› ወይም ‹የተአምራት አድራጊነት› ጥማት ለማርካት ሲባል የሚከናወኑ አልነበሩም። እንዲያውም፥ ሰዎች በተአምራት አድራጊነቱ ላይ እያተኮሩ ሲመጡ፥ ጌታ ያለበትን ስፍራ ለቆ የሚሄድ ከመሆኑም በላይ፥ ያደረጋቸውን የፈውስ ተአምራት እንዳይናገሩ ሕዝቡን ያስጠነቅቃቸው ነበር (ማርቆስ 1:32–38፤ 1:44)። ይህ በዛሬው ዘመን ምን ያህል ሰው "እንደ ፈወሱ" በማሳየት ሌሎችን ለማስደነቅ የቪድዮ ካሜራ ለሚያንጓጉ ግለሰቦች ትልቅ ትምህርት ሊሆናቸው ይገባል።

- የኢየሱስ ተአምራት መሢሕነቱን የሚያረጋግጡ ቢሆኑም፥ ብዙ ሰዎች በተአምራቶቹ እገዛ ወደ እምነት ሊመጡ አልቻሉም ነበር። እንዲያውም፥ ተአምራቱን ለሥጋዊ ጥቅም፥ ለእንጀራ መብያ ይጠቀሙት ነበር (ዮሐንስ 6:30–48)።
- ኢየሱስ በይበልጥ ያተኩር የነበረው በደኅንነት ተአምር ላይ ነበር። ሰዎች አንድ አስደናቂ ነገር አይተው ከሚደነቁ ይልቅ፥ የሕይወት መዳን ማግኘታቸው ከሁሉም እንደሚልቅም ተናግሯል (ሉቃስ 10:21)። ለዚህም ምክንያቱ ሥጋዊ ፈውስም ሆነ መሰል ምድራዊ ችግር ማቃለያ ተአምራት ጊዜያዊ መፍትሔዎች ሲሆኑ፥ የነፍስ መዳን ግን እንከን ከሌለው ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ጋር የሚያዛምደን መሆኑ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓይነት ሁኔታ አገልግሎቱን ፈጽሞ ወደ አብ ቀኝ ሲሻገር፥ ሐዋርያት እርሱ የጀመረውን ሥራ ቀጥለው ነበር። ጌታ በዮሐንስ 14:12፥ ደቀ መዛሙርቱ ከርሱ የበለጠ ሥራ እንደሚያከናውኑ በተናገረው መሠረት፥ ሐዋርያቱ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ፈውስና ተአምራት ጭምር በከፍተኛ ደረጃ ሲያካሂዱ ቆይተዋል። ለመሆኑ፥ ጌታ "ከኔ በላይ" ትሠራላችሁ ሲል ምን ማለቱ ነው?

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ መምህር በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገር፥ "መቼም ከሐዋርያቱ በሁለት ዓሣና በአምስት እንጀራ አምስት ሺህ ሕዝብ አብልቶ ያጠገበ አልነበረም፤ ከዓሣ ውስጥ የቀረጥ ገንዘብ ያወጣም አልተጻፈም" ብሏል። ይኸው ሰው አሳቡን በመቀጠል፥ ጌታ የተናገረው ሐዋርያቱ በመጠንና በጥልቀት ከርሱ የላቁትን ተአምራት እንደሚሠሩ ሳይሆን፥ ይልቁንም እነርሱ ብዙዎች እንደመሆናቸው በርከት ያሉ ተአምራት እንደሚሠሩ ነው ሲል አጠቃሏል። ኢየሱስ ሥጋ ለብሶ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረ ጊዜ መድረስ፥ ማገልገልም ሆነ ተአምራት ማድረግ የቻለው ይመላለስ በነበረው የገሊላ አካባቢ ነበር። ሐዋርያቱ ግን በዓለም ዙሪያ ሁሉ ቃሉን ብቻ ሳይሆን፥ ፈውሱንና ተአምራቱን ጭምር ይዘው ይዞሩ ነበር። ለዚህም ነው ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ብዙ ተአምራት እንዳዩ የጻፈላቸው (ገላትያ 3:5)።

በሐዋርያት ሥራ ውስጥ ከፍተኛ የፈውስና የተአምራት ታሪኮች ተመዝግበው እንመለከታለን። የጴጥሮስ ጥላ እንኳ ፈውስን ያስገኘበት ሁኔታ በሐዋርያት ሥራ 5:12–16 ውስጥ ተጠቅሶ ይገኛል። ይሁንና፥ የሐዋርያት ዋንኛ ትኩረት ፈውስና ተአምራት ማድረግ ሳይሆን፥ ወንጌልን ማሰራጨት ነበር። እነዚህ ተአምራዊ ክስተቶች በእግረ–መንገድ የሚከናወኑ አስደሳች ገጽታዎች ነበሩ።

በዚህ ጉዳይ ላይ ጥናት ያደረገ አንድ ጸሐፊ እንዳጤነው፥



ከሐዋርያት ሥራና ከመልእክቶች ስለ ፈውስና ስለ ተአምራት የሚከተሉትን እውነቶች እንመለከታለን።

- ተአምራት በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ በተደጋጋሚ ይታዩ ነበር።
- ደቀ መዛሙርቱ ኢየሱስ ያደረገውን ያህል ብዙ የተለያዩ ተአምራት አድርገዋል። እነዚህም ተአምራት ፈውስ፥ ከሙታን ማስነሣት፥ ከአጋንንት ነጻ ማውጣት የመሳሰሉ ነበሩ።
- ሐዋርያትም እንደ ኢየሱስ ትኩረታቸውን ያደረጉት ቃሉን በማስተማሩና በወንጌል ስርጭት ላይ እንጂ፥ ሕዝብን ጉድ ያሰኘ ተአምር በመሥራቱ ላይ አልነበረም። ተአምራትን ይመለከቱ የነበሩት እንደ አገልግሎታቸው ክፍል እንጂ፥ እንደ ዛሬዎቹ አገልጋዮች ለራሳቸው ዝናና ክብር ለማግኘት አልነበረም።
- የሐዋርያት ተአምራት ጌታ ከእነርሱ ጋር ሆኖ በመሥራት ላይ እንደሚገኝ ለማሳየት ያገለግሉ ነበር። የሚሠሩትና የሚያደርጉትም ከእግዚአብሔር እንደሆነ ለሰዎች ለማሳየት አገልግለዋል (ገላትያ 3:5)።
- ሐዋርያቱ ለሚያከናውኗቸው የፈውስና የተአምራት ሥራዎች ከማንም ሰው ገንዘብ ያልተቀበሉ ሲሆን፥ ስምዖን ለሚፈልገው ሁሉ መንፈስ ቅዱስን በማደል ገንዘብ ለማግበስበስ ፈልጎ እነ ጴጥሮስን ባነጋገረ ጊዜ፥ ጴጥሮስ በከፍተኛ ደረጃ እንደ ተቆጣው ተገልጾአል (የሐዋርያት ሥራ 8:9–24)።
- ሐዋርያትም እንደ ኢየሱስ አንድ ሰው እንደሚፈወስ ከተናገሩ፥ ሰውየው ያለምንም ቅድመ–ሁኔታ ይፈወስ ነበር። ግማሽ ፈውስ ወይም ያልተሳካ ፈውስ የሚባል ነገር በሐዋርያት አገልግሎት ውስጥ አልነበረም።
- በአንድ ሰው የመፈወስ ችሎታና ፈውሱን በሚቀበለው ሰው እምነት መካከል ቀጥተኛ ግንኙነት ስለ መኖሩ በግልጽ የተጠቀሰ ነገር የለም። ሐዋርያት ተአምራት ለማድረግ አስበው ተአምራቱ የሚደረግለት ሰውዬ እምነት በማጣቱ ተአምራቱ የተስተጓጎለበትም ጊዜ አልተጠቀሰም።
- ሐዋርያት ተአምራትን ለራሳቸው ጥቅም ያዋሉበት ጊዜ የለም። እንደዚሁም፥ ሐዋርያት የታመሙትን ሁሉ እንዳልፈወሷቸው ልብ ማለቱ ተገቢ ነው። ለምሳሌ፥ ከጳውሎስ ጋር ለማገልገል ከመጡት ሰዎች መካከል አፍሮዲጡ በከፍተኛ ድረጃ ታሞ፥ ጳውሎስ ሊፈውሰው ቢፈልግም እንኳ አልቻለም ነበር (ፊልጵስዩስ 2:27)። ለራሱም እንኳ ፈውስ ሊያመጣ አልቻለም ነበር (2ኛ ቆሮንቶስ 12:7–10)። ስለሆነም፥ ክርስቲያኖች ሁሉ በጤንነት መኖር እንዳለባቸው የሚያመለክት ምንም ፍንጭ እንደሌለ እንመለከታለን። ክርስቲያኖችም እንደ ማንኛውም ሰው ምድራዊ ችግርችን ከመጋፈጥ እንደሚያመልጡ የሚያሳይ መረጃ የለም – ይህ የሰው ልጅ ከንቱ ምኞት ብቻ ነው – የፍጹም ዓለም ምኞት።
- በሐዋርያት መጽሐፍ ውስጥ ከተፈጸሙት ተአምራት አብዛኞቹ በቤተ ክርስቲያን ምሥረታ አካባቢ የተከናወኑ ናቸው። ብዙውን ጊዜ ተአምራት በብዛት የሚፈጸሙት ቤተ ክርስቲያን ገና ወደ ብስለት ከመድረሷ በፊት ነው።

የተሰባሰቡበትን ቤተ ክርስቲያን "የወንበዴዎች ዋሻ" ሲሉ የገለጹት።

ችግሮችን ተጋፍጦ ማለፍ የማይሆንላቸው ብዙ ሰዎች ይህንኑ አግራሞ ይጠቀማሉ። ግን ግን እዚያም የምንሄደው ሰዎች ዘንድ መሆኑን ልብ ማለቱ የሚሻል ይመስለኛል።

በቅርብ የማውቀው አንድ አገልጋይ፥ ከአዲስ አበባ ወጣ ብላ በምትገኝ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አገልግሎት ጀመረና ብዙም ሳይቆይ "እነርሱ አይረቡም!" ብሎ እዚሁ አዲስ አበባ መጣ። እዚህም አንዲት ዓመት እንኳ ሳያገለግል የተሰጠውን ቅጣት አሻፈረኝ ብሎ ወደ እነ ሐገን ትምህርት ፊቱን መልሷል።

3. ሌላው ችግር ለአገልግሎት መቸኮል ነው። ብዙውን ጊዜ አንድ የአገልግሎት ሸክም ያለባቸው ሰዎች ዛሬውኑ ለመሰማራት ሲሞክሩ፥ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ "ቆይ . . . ረጋ በል . . ." ትላለች። እናም ውዝግብ ይነሣል።

4. ከአምልኮ ሥርዓት ጋር የተያያዙ ችግሮች። በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የአምልኮ ሥርዓት የግድ ቀዝቀዝ ማለት አለበት። በሌሎች ደግሞ ሞቅ-ደመቅ ያለ! እናም የቤተ ክርስቲያኒቱ የአምልኮ ሁኔታ ደስ ያላላቸው ሰዎች ለመለወጥ ሞክረው፥ "ጥርስ ከገቡ" "እግረ-አውጪኝ!" ለማለት ይገደዳሉ።

   እንደኔ እንደኔ፥ ለሁሉም ሰው የሚስማማ የአምልኮ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ባይቻልም፥ መጽሐፍ ቅዱሳዊና ለምእመናን ልብ የሚደርስ ማፋጭ አገልግሎት ማቅረቡ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ድርሻ ሊሆን ይገባል። ምእመናኑ የልባቸው እንቅቅልሽ ሳይፈታ እንዲሁ ቤተ ክርስቲያን ደርሰው የሚመለሱ ከሆነ፥ አሁንም ሆነ ወደፊት የመንፈስ ቅዱስ ዳሰሳ ከማይታይበት ጉባኤ መሸሻቸው የማይቀር ነው። መንፈስ ቅዱስ ከማይመላለስበት ጉባኤ ምን ሊገኝ?

5. አዲስ መንፈሳዊ ልምምድ መሻት። (ይኼ ከላይኛው አሳብ ጋር የሚሄድ ነው።) መቼም ሰው ካለበት ተደላድሎ የሚቀመጠው ውስጡ ሰላም ካለው ነው። ውስጡ ባዶ ከሆነ ግን ሌላ ነገር መፈለጉ የማይቀር ነው። እናም ብዙ ሰዎች ቤተ ክርስቲያናቸው የሚፈልጉትን ዓይነት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ካላሳየች፥ ወደ ሌላ ያመራሉ። ለምሳሌ፥ ቀደም ብለን እንደ ተመለከትነው፥ የእምነት እንቅስቃሴ መሥራች የሆነው ኬንየን የነ ክርስቲያን ሳይንስን ንድፈ-አሳብ ወደ ቤተ ክስቲያን ይዞ የመጣው እንዲህ ዓይነቱን የቤተ ክርስቲያን ድርቀት ለማርጠብ ነበር።

## *የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ምን ይሆን?*

ከላይ የተመለከትናቸውና ሌሎችም ችግሮች ተዳምረው ምእመናንን ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ያቅበዘብዛሉ። በእኔ እምነት ቤተ ክርስቲያን ይህንኑ ችግር ዝም ብላ ልትመለከት የሚገባት አይመስለኝም። የጉዳዩ ቀጥተኛ ባለቤት ናትና።

አንዳንዶች የተሻለ ነገር ፍለጋ ሲሄዱ፥ የከፋ ነገር እንደሚጠብቃቸው አይገነዘቡም። ስለሆነም፥ ቀዳሚው የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ሚዛናዊነቱን የጠበቀ ስብከትና ትምህርት በሚገባቸውና በሚጥማቸው መንገድ ማቅረብ ሊሆን ይገባል ብዬ አምናለሁ። ይህ ግን ባብዛኛው ሲከሰት አንመለከትም።



የእምነት እንቅስቃሴ ከመከሰቱ በፊት ስንቶቻችን ነን ስለ ሙዓለ-ንዋይ የቀረበ ትምህርት ወይም ስብከት የሰማን? ጌታችን ከተናገራቸው ምሳሌዎች ብዙዎቹ ስለ ገንዘብ የሚያነሡ ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ግን እንዲህ ዓይነቱ ጠቃሚ ነገር ችላ ተብሎ እንመለከታለን። እናም አንድ ብር በመስጠት መቶ ብር ታተርፋለህ ለሚሉን የምንሰጣቸው መልስ አይኖረንም። ከዚያ ይባስ ደግሞ ነገሩ እውነት መስሎን እንከተላለን።

እኔ እንደማምነው፥ ጳውሎስ እንዳደረገው "የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ"(የሐዋርያት ሥራ 20:27) ለማስተማር ቀናው መንገድ፥ ደስ ያለንን ርእሰ-ጉዳይ እየመረጡ መስበኩ ሳይሆን አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መርጦ ማስተማሩ ነው። አንድ ወር ወይም ሦስት ወር ቢወስድ ምንም አይደለም። የጌታን ቃል በዓውዱ (contextually) እንግር ከተባለ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው።

በሌላ በኩል የማስተማሪያ ዘዴዎቻችንም ሊዳብሩ ይገባል። ሁልጊዜም አንድ ሰው ምስባኩ ላይ ለሁለት ሰዓታት ከሚቆም፥ እንደ የመድረክ ውይይት ወይም ፓናል ዲስከሽን፥ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ፊልሞች፥ ወዘተ. በመጠቀም፥ አድማጮቻችንን ልንደርስ እንችላለን። ሥነ-ጽሑፍና ድራማም በጥሩ ሁኔታ ከተሠራበት ጠንካራ የመልእክት ማስራጫ መንገድ ይሆናል። እኔ እንደ ማምነው፥ መንፈስ ቅዱስ ስብከትን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም የማስተማር መንገድ የመጠቀም ችግር የለበትም። የለም፥ ስብከት ብቻ ነው የማምንበት የሚል ካለም እንደ ተረዳው ያድርግ። ዋናው ግን መንጋውን ለተኩላዎች ላለመስጠት ይትጋ።

የአገልግሎት ችግርን በተመለከተ፥ የጌታ መንፈስ በመራቸው መጠን እውነተኛ ስጦታ እንዳላቸው ካወቁ፥ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ደጅ ባያስጠኗቸው እመርጣለሁ። ገና "ጀርባ እስኪጠና" ተብሎ የአገልጋዩ የልጅነት ጉልበት እስኪዝል ማስጠበቁ የሚበጅ አይመስልም።

ስለሆነም፥ ከጽዳት ጀምሮ ያሉትን አገልግሎቶች ቀስ በቀስ ቢያስለምዷቸው መልካም ነው። እናገለግላለን ብለው የመጡትም ሰዎች "ካለ ስጦታዬ!" ብለው ባይጓጉቱና በተሰጣቸው ታምነው ወደ ቀጣዩ አገልግሎት ቢሸጋገሩ ይበጃል ባይ ነኝ። ለጌታ መቼም አገልግሎት ሁሉ አገልግሎት ነው! በርሱ ዘንድ ትልቅና ትንሽ የሚባል አገልግሎት የለም። በርሱ ዘንድ የጽዳት ሠራተኛ ሃምሳ ብር፥ ሰባኪ ደግሞ ሺህ ብር የሚባል የለም። በተሰጠን መክሊት በታማኝነት እስከ ሠራን ድረስ በቂ ነው። የታይታ ታማኝነት ሳይሆን፥ የልብ ታማኝነት!

አስቀድመው የአገልግሎት ወንበር የያዙትም ደግሞ ለሌሎች የማስተላለፍ ኃላፊነት እንዳለባቸው ልብ ሊሉ ይገባል። አለቃ ሆኜ ስለማላውቅ፥ አለቅነት ወይም ሥልጣን ምን ያህል እንደሚጥም አይገባኝም። እንደሰማሁት ግን እስኪወጡ ያስፈራል እንጂ ከወጡ ወዲያ ልቀቅ አይልም አሉ። ልቀቅ አለ አትልቀቅ የተቀመጥነው ለማገልገል ነውና ሁልጊዜም የተሻለ ለሚያገለግል ልናስረክብ ይገባል። ቃለ ሕይወት መጽሔት "አከራካሪው ሰው" ሲል የሰየመው ዶክተር ብንያሚን ዩሱፍ እንዲህ ዓይነቱን ሁኔታ በመንቀፍ፥ "አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ካልሞቱ፥ ወጣቶቹ ሹመት አያገኙም!" ሲል ተደምጧል።

አንዳንዶች በተለይ ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ጡረታ የወጡ እንደሆነ ከቤተ

## የአሳብ ሥርቆት (Plagiarism)

ከነት ሐገን ከከንየን ጽሑፎች ገልብጦ ሲያበቃ የራሱ አስመስሎ ስላቀረባቸው አሳቦች ቀደም ብለን ተነጋግረናል። ይህም ሐገን የከንየንን አሳቦች በመሥረቅ (plagiarism) አግባብነት የጎደለው ተግባር እንደፈጸመ የሚያሳይ ነው። ምንም እንኳ የዚህ ዓይነቶቹ የሥርቆት አሳቦች እጅግ በርካታ ቢሆኑም፥ ለአብነት ያህል የሚከተሉትን አቅርበንላችኋል።

| <u>Kenneth Hagin</u> | <u>E. W. Kenyon</u> |
|---|---|
| *The 22nd Psalm gives graphic picture of the crucifixion of Jesus_ more vivid than of John, Matthew or Mark who witnessed it.* | *The twenty-second Psalm gives a graphic picture of the crucifixion of Jesus. It is more vivid than of John, Matthew or Mark who witnessed it.* |
| *He utters the strange words "But thou art holy." What does that mean? He is becoming sin.... His parched lips cry, "I am a worm and no man." He is spiritually dead_the worm. Jesus died of a raptured heart. When it happened, blood from all parts of His body poured through the rent into the sack which holds the heart. As the body cooled, the red corpuscles coagulated and rose to the top, the white serum settled to the bottom. When that Roman spear pierced the sack, water poured out first, then the coagulated blood oozed out, rolling down his side onto the ground. John bore witness of it. ("Christ Our Substitute," The Word of Faith (Maar., 1975, pp. 1, 4, 5, 7).* | *He says the strongest words, "But thou art holy." What does mean? He is becoming sin. Can you hear those parched lips cry, "I am a worm and no man"? He is spiritually dead. The worm. Jesus had died of ruptured heart. When that happened blood from all parts of the body poured in through the rent, into the sack that holds the heart. Then as the body cooled, the red corpuscles coagulated blood oozed out, rolled down His side onto the ground, and John bore witness of it. (What Happened from the Cross to the Throne (Seatle: Kenyon's Gospel Publishing Society, 1969), 44-45).* |
| *What does Identification mean?* | *At once you ask, "What does identification mean?"* |
| *It means our complete union with Christ.* *This gives us the key which unlocks the great teaching of identification. Christ became one with us in sin that we might become one with him in righteousness. He became as we were to the end that we might become as he is now. He died to make us live. He became weak to make us strong. He suffered shame to give us glory. He went to hell to take us to heaven.* | *It means our complete union with him in his substitutionary sacrifice. This gives us the key that unlocks the great teaching of identification. Christ became one with us in sin, that we might become one with him in righteousness. He became as we were to the end that we might become as he is now ... He died to make us live ... He became weak to make us strong. He suffered shame to give us glory. He went to hell to take us to heaven.* |
| *He was condemned to justify us. He was made sick that healing might be ours. (The Resurrection! What gives Us... "The Word of Faith Apr., 1977, p. 5).* | *He was condemned to justify us. He was made sick that healing might be ours. (Identification: A Romance in redemption (Seatle: Kenyon's Gospel Publishing Society, 1968], 6,7).* |
| *Here is the picture of Christ. In awful combat with the hosts of darkness. It gives us a glimpse of the tremendous victory He won before He rose from the dead. The margin of King James reads, "He put off from himself the principalities and the powers." It is quite obvious and evident that the whole demon hosts, when they had Jesus in their power intended to swamp him , to overwhelm him, and to hold Him in fearful bondage. But the cry came from the throne of God that Jesus had met the demands of justice, that the sin problem had been settled, that man's* | *The picture here is of Christ... in awful combat with the hosts of darkness. It gives us a glimpse of the tremendous battle and victory that Jesus won before he rose from the dead. The margin reads, "Having put off from Himself the principalities and powers." It is evident that the whole demon host, when they saw Jesus in their power simply intended to swamp Him in fearful bondage until the cry came forth from the throne of God that Jesus had met the demands of justice; that the sin problem was settled and the man's redemption was a fact.* |

*illuminative prayers of the Old Testament. Abraham was taking his place in the covenant, received rights and privileges which we very little understand. The covenant Abraham had just solemnized with Jehovah gave him a legal standing with God ... We hear him speaking so plainly..."shall not the judge of all the earth do right?" All through the Old Testament we find men who understood and took their place in the covenant. Joshua could open the Jordan. He could command the sun, moon and stars to stand still in the heavens. Elija could bring fire out of heaven to consume the altar as well as the sacrifice.*

*David's mighty men were utterly shielded from death in time of war as long as they remembered the covenant. (Plead Your Case, Tulsa: Faith Library, 1979, pp. 4-9; cf. pp. 23-32.)*

*Man is a spirit who possesses a soul and lives in a body...He is in the same class with God ... We know that God is a Spirit. And yet [He] took upon himself a man's body ... He is in the same class with God. We know that God is a Spirit. And yet [He] took upon Himself a man's body....When God took upon Himself human form, He*

*and suggestive prayers in the Old Covenant ... Abraham was taking his place in the covenant. Abraham had through the covenant received rights and privileges that we little understand. The covenant that Abraham had just solemnized gave him a legal standing with God. We hear him speak so plainly, "shall not the judge of all the earth do right?" All through the Old Covenant we find men who understood and took their place in the covenant. Joshua could open the Jordan. He could command the sun, moon and stars to stand still in the heavens. Elija could bring fire out of heaven to consume the offerings as well as the altar.*

*David's mighty men were utterly shielded from death in their wars. They became supermen as long as they remembered the covenant.(The Two Kinds of Faith, Seattle: Kenyon's Gospel Publishing Society, 1969, pp. 76-84.)*

*Man is a spirit being, he has a soul and he lives... in a body ... He is in the same class with God ... We know that God is a Spirit. And yet [He] took a body. upon himself a man's body.... He is in the same class as God. We know that God is a spirit and He became a man and took on a man's body...He was no less God than He was*



*was no less God than when He didn't have a body. Man, at a physical death, leaves his body. Yet he is no less man than he was when he had his body. (Man of Three Dimensions, Tulsa: Faith Library, 1973].)*

*before He took the physical body ... Man, at death, leaves his physical and is no less man than when had his ... body. (The Hidden Man[Settle: Kenyon's Gospel Publishing Society, 1970], p. 40; Two Kinds of Faith, p.3).*

## ማስታወሻዎች/Notes

1

1. Tom Carter, "Religion Without Hope: Kenneth Hagin's Ministry doesn't Need the Spotlight," p. 5.
2. Charles Capps, taped correspondence, Feb. 17, 1982.
3. Gorden Fee, "Some Reflections on Current Disease," pp. 12-16.
4. Steven Lawson, "Faith Preacher Hobart Freeman Dies," Charisma (Feb. 1985), p. 110.
5. Phone interview with Joseph Flower, general secretary to the Assemblies of God, Springfield, Mo., March 17, 1986.
6. Vinson Synan, "Faith Formula Fuels Charismatic Controversy," Christianity Today 24(Dec. 12, 1980), pp. 65-66.
7. Jimmy Swaggart, "The Balanced Faith Life," pp. 3-4.
8. "The Balanced Faith Life, part 2," p.11.
9. Jimmy Swaggart, Hyper Faith, pp. 43-44.
10. "Code of Ethics," The Network, p.7.

2

1. Kenyon, Jesus the Healer, p.17; cf., Kenneth Hagin, Seven Things You Should Know About Divine Healing, pp. 13-15.
2. Kenyon, Hidden Man, p.47.
3. Kenyon, What Happened, p.47; cf., Hagin, Christ our Substitute, pp. 1,4.
4. Fredric K.C. Price, Ever Increasing Faith Messenger.
5. Personal letter from Kenneth Copeland.
6. Eddy, Science and Health, p.30.
7. Hagin, The Name of Jesus, p.32.
8. Copeland, What Happened from the Cross to the Throne(Tape).
9. Kenyon, What Happened, p. 12.
10. Kenyon, Identification, pp. 6,7; cf., Hagin, The Resurrection: What it gives Us, p.5.
11. Kenyon, Hidden Man, p.26
12. Kenneth Hagin, Zoe: The God-Kind of Life, p. 42.
13. Hagin, Walking in The Light of Life.
14. Hagin, Walking in The Light of Life.
15. Hagin, The Virgin Birth, p.8.
16. Hagin, Zoe, p.41.
17. Hagin, The Name of Jesus, p. 105.
18. Ibid., p. 20.
19. Trine, In Tune, p. 21.
20. Erickson, Christian Theology.

3

1. Hagin, How to Write Your Own Ticket with God, pp. 5, 20, 21.
2. Hagin, "The Law of Faith," Word of Faith(Nov., 1974).
3. Hagin, Having Faith in Your Faith, pp. 3-4.
4. Frederick K.C. Price, How Faith Works, pp. 110-111.
5. Hagin, The Name of Jesus, p.16.

4.

1. Kenneth Hagin, Healing Belongs to Us, pp. 16-17.
2. Kenyon, Identification, p. 15.
3. Kenyon, Jesus the Healer, p. 81.
4. Hagin, "Looking at the Unseen," word of Faith (June 1974), p. 2.
5. Trine, In Tune, p. 112.
6. Ibid., p. 25.

7. Kenyon, Jesus the Healer, p. 44.

8. Ibid., p. 67.

9. Trine, In Tune, p. 65.

10. Kenyon, Power of Positive Confession, p. 119.

11. Ibid., p. 80.

12. Trine, In Tune, p. 66.

13. Kenyon, Jesus the Healer, p. 26.

14. Kenneth Hagin, The Real Faith, p. 13.

15. Kenyon, Hidden Man, p. 107.

16. Hagin, Real Faith, pp. 19-20.

17. Price, Faith, Foolishness, or Presumption? pp. 76-77.

18. Eddy, Science & Health, p. 495.

19. Ibid., 417.

20. Ibid., 412.

21. Ibid., 420.

22. Kenneth Hagin, God's Medicine, pp. 17-18. Kenneth Copeland, The Laws of Prosperity, p. 22.

23. Frederick Price, Is Healing for All? p. 113.

24. Price, How Faith Works, pp. 92-93.

25. Kenyon, Jesus the Healer, p. 65.

26. Hagin, "Healing: The Fathers Provision," Word of Faith, p. 9.

27. Price, Is Healing for All? p. 104.

28. Fred Price, Ever Increasing Faith messenger, p. 3.

29. Ibid.



5

1. Stephen Strang, "a Pastor Dares to Face Aparheid," Charisma(June 1988), 63-66.

2. William W. Menzies, "Will Christians go Cultic?" Christianity today(Mar. 3, 1989), pp. 59-60.

3. Jerry Horner, "Faith teaches Under Siege," Charisma & Christian Life(Feb., 1989), p.38.

4. McConnell, "Letters to the Editor," (Jan./Feb., 1992), p. 13

5. William DeArteaga, Quenching the Spirit, p. 293.

6. Ibid., pp. 228-229

7. Ibid., p. 212

8. Ibid., p. 200

9. Ibid., 227

10. Ibid., 211

6

1. Hagin, Jr., "Trend toward the Faith Movement," p.67.

2. Fred Price, taped correspondence, Inglewood, Calif., Feb. 18, 1982.

3. John Osteen, taped phone interview, Pastor of Lakewood Outreach center, Houston, Tex., Feb. 24, 1982.

4. Ruth Kenyon Houseworth, taped phone interview, Lynwood, Wash., Feb. 19, 1982.

5. John Kennington, "E. W. Kenyon and the Metaphysics of Christian Science," unpublished written statement, Portland, Ore., July 8, 1986.

6. Ibid.

7. Kenneth Hagin, The Name of Jesus(Tulsa: Faith Library, 1981), preface.

8. Hagin, The Name of Jesus, preface.

12. Trine, In Tune, p. 53.

13. Ibid., p. 54.

14. Kenyon, The Hidden Man, p. 158.

15. Trine, In Tune, p. 36.

16. Constitution & By-Laws, p. 168.

17. Rudolf Bultman, "Gingko," 1:692-96.

Bibliography


- Beverly, James. Holy Laughter & The Toronto Blessing, Grand Rapids: Zondervan, 1995.
- Bruno, Michael. Christianity in Power, Abba Ministries, 1994.
- Stott, John. The Letters of John, Grand Rapids: Eerdmans, 1995.
- Canty, George. The Hallmarks of Pentecost, London: Marshal Morgan & Scot.
- McConnel. A Different Gospel

Mariarity, Michael, A New Charismatics, Grand Rapids: Michigan, 1992.